PANORAMA # 12

## የትዝብት አድማስ

**ጥር** 30 2000 **ዓም**

## ዛሬ ሀገር ወዳድ መሪዎች የት ናቸው?

***ሀገራችን ኢትዮጵያ እስከዛሬ ድረስ ኅልውናዋን ጠብቃ ልትቆይ የቻለችው÷ ሀገሩን ወዳድ የሆነውን ዜጋ በማስተባበር ከውጭ አጥቂ ጠላቶች ሊመክቱ በቻሉ ሀገር ወዳድ መሪዎች እንደነበር የታሪክ ማስታዎሻ አቅርቡለት የሚባል ጉዳይ አይደለም። በተለያዩ የታሪክ ሂደቶች የተፈራረቁት የኢትዮጵያ የሩቅና የቅርብ ዘመናት መሪዎች÷ በአገዛዝ ዘመናቸው÷ የተለያዩ ዕፀዖችና ጉድለቶች ያሳዩ ቢሆንም÷ በአንድ ነገር ግን የማይጠረጠሩ እንደነበር የሚካድ አይሆንም። አነሰም በዛ÷ የሀገራቸውን ክብር÷ ነፃነት÷ የግዛት አንድነትና ዳር ድንበር በማስጠበቅ በኩል ሁሉም ቀናዒ የነበሩ መሆናቸው ነበር። ከአቅማቸው በላይ ካልሆነባቸው በስተቀር ሆን ብለው ወይም በስንፍና ያለዚያም በፍርሃትና በግል ጥቅም የሀገራቸውን ክብር አልሸጡም÷ አላዋረዱም÷ ነፃነቷን አላስደፈሩም። ይህን ከማድረግ የዕለት ሞታቸውን በመምረጥ የክብር ሞትን ሞተው በአርዓያነት አኩሪ ታሪክ አስመዝግበው አልፈዋል። አሁን ለአለውም ትውልድ የታሪክ መመኪያ ጥለው ሄደዋል። የመቅደላ÷ የዶጎአሌ÷ የመተማና የአድዋ ጦርነት ታሪኮች ያስመዘገቡት ዜና-መዋዕል እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።***

***ይህ ዜና መዋዕል ግን ከመቶ ዓመት ወዲህ ያለውን ታሪክ በዚህ መልኩ አልመዘገበውም። በተቃራኒው መልኩ ካልሆነ በስተቀር! ከባህልና ከታሪክ አኳያ ሲታይም ÷መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ÷ ጠንካራ ዕምነት በሀገሩ ላይ ስለ ነበረው÷ከዚህ ዕመነት የመነጨ የሀገር ወዳድነት ባኅርይና ዕመነትን ሊመሠረት ችሏል። በየፊናቸው መንበረ-ሥልጣናቸውን የወረሱትና ቅብዓ-መንግሥት የተቀናጁት በዕምነታቸው ሳቢያ ከላይ ከሰማይ የተሰጣቸው ክብርና ኃይል ነው ስለሚባልላቸው÷ ሀገርን መክዳትና ሕዝብ ለጠላት አጋፍጦ መሰወርን እንደ ሞትና ውረድት ስለሚቆጥሩት ከሞላ ጎደል ይህንን ሳያደርጉ አለፈዋል።***

***ይህም ስለተባለ÷ አስተዳደራቸው ዕፁብ ድንቅ÷ መንግሥቶቻቸው ሀሴትና ፍስሀ የተሞላበቻው÷ ፍርዳቸው የተስተካከለ÷ ማለት አልነበረም። ይህም መሆን ነበረበት ተብሎም አይጠበቅም። ምክንያቱም÷ ከጉልታዊ ሥርዓት ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ይገኛል ተብሎ ስለማይታሰብ ነው። ዛሬም***

በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ያለችው ኢትዮጵያ እንኳ ከንጉሣዊ ፈላጭ ቆራጭነት ወደ አንድ ብሔር ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ወደቀች እንጅ፥ ወደ ተሻለና ወደ መልካም አስተዳደር አልተሸጋገረችም። ይልቁንም የዛሬዎቹ መሪዎች ከሀገር ወዳድነት ወደ ሀገር አጥፊነትና ወደ ሕዝብ ጠላትነት የተለወጡ ግለሰቦች ናቸው። እዚህ ላይ በሀገራችን ዛሬ አንድ የታሪክ ምፀት እንደተከናወነ እንገነዘባለን። ብሔራችንን ከኢትዮጵያ ገንጥለን የራሳችንን ሪፑብሊክ መሥርተን የተለየች ሀገር እንፈጥራለን ብለው እነ ወያኔ ከተነሱበት ከኢትዮጵያ የትግራይ መሪት የተፈጠሩት አጤ ዮሐንስ አራተኛ (ራባአይ) ከዛሬ መቶ ዓመታት በፊት፥ የማኅዲስቶችን ወረራ ለመመከት ሲሉ ገላባት ላይ

ባደረጉት የጀግንነትና የሀገር ወዳድነት ባኅርይ፥ ልክ አንድ አንድ ተዋጊ ወታደር በመጀመሪያው የውጊያ መስመር ተሰልፈው ድርቡሾቹን ሲረፈርፉ ከጠላት ወገን በተተኮሰች ጥይት ተመትተው መውደቃቸውን የተመለከቱ ጠላቶች፥የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት አስክሬን ማርከው በመውሰድ አንገታቸውን ቆረጡት። ወደ ሱዳኗ ኦምዱርማን ከተማ በመውሰድም በእንጨት ላይ በመስቀል ተሳለቁበት። ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ የተፈጠሩት እነ መለስ ዜናዊ፥የአጤ ዮሐንስን አንገት ከቆረጡት ሰዎች የልጅ ልጆች ጋር በመመሳጠርና ከእነኝህም በተሰጣቸው ጦር መሳሪያ ሀገራቸውን እንደ ውጭ ጠላት ወረሩ፥አጠቁ ፥የሱዳን ባለሰልጣኖችን የቆየ ፍላጎትም አሳኩላቸው። ከዚህስ የበለጠ የታሪክ ምፀት ምን ሊገኝ ይችላል? ጀግናው የትግራይ ሕዝብ በአኩሪ ታሪኩና ስሙ የተፈፀመውን የታሪክ ምፅት እንደተገነዘበው አንጠራጠርም!!

ታዲያ ይህንን የታሪክ ምፀትና በደል የሚመለከተው ይህ የዛሬው ትውልድስ ስለ ሀገሩ ምን ይሰማዋል? ሀገር ወዳድ መሪ የሌላት ሀገርስ የወደፊት ዕድሏ ምን ሊሆን ይችላል? እረ ለመሆኑ ሀገር ወዳድ መሪዎች ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? ሀገር ወዳድነት መጠኑና ወሰኑ እስከምን ድረስ ይደርሳል? ሀገር ወዳድነትስ እንዴትና በምንስ ሊገለጽ ይችላል? እነኝህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እየጠየቁ በሚገኙት መልሶች ምናልባት አንድ የጋራ ግንዛቤና መግባባት ሊገኝ ይችላል ብለን እንገምታለን። ከዚህም ግንዛቤና መግባባት ሊደረስ የሚቻለው፥ ሁሉም በየግሉ፥ኢትዮጵያን እንደ አንድ ሀገር፥ ዜጎቿንም እንደ አንድ ሕዝብ መኖር አለባቸው ተብሎ ከልብ ሲታመንበት ብቻ ነው። እነኝህን ጥያቄዎች ሊያስነሱ የቻሉት ምክንያቶችና ሰበቦች፥ ለአለፉት አስራ ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ እየጨቆኑ በሚገዙት ጎጠኛ ቡድኖች በዘረጉት የዘረኝነት ፖሊሲ ሳቢያ ነው። የሀገር ወዳዳነት ስሜት የሚመነጨው ከልብ ከተመሠረተ የሕዝብና የሀገር ታማኝነት ነው ። ያልተከፋፈለ፥ ያልተደበላለቀ፥ያልተመሰቃቀለና ያልተሸራረፈ ታማኝነት መኖር ለሀገር ወዳድነት ባሕርይና ቁርጠኝነት ወሳኝ ነው። "ከወገብሽ በታች ሚስቴ ከወገብሽ በላይ እህቴ" በሚል ከተከፋፈለና ሁሉም አይቅርብኝ ዘማዊነት ከሚመነጭ ታማኝነትና ፍቅር ሊመጣ ከቶ አይችልም። አንድን ሀገር በዘር በሚከፋፍል ፖሊሲ እየገዙ፥ብሔራዊ ስሜትና የሀገር ፍቅር ቁርጠኝነት

ይመጣል ተብሎ መመኘት ዘበት ነው። ይልቁንም፥ ሁሉም በየፊናዊ የማንነት ፍለጋ ለማካሄድ ሲሯሯጥና ሲባዝን ነው የሚኖረው። በልዩነት አንድነት፥ በንዑስነት ዓቢይነት፥ ከትንሽነት ወደ ታላቅነት፥ ከጠባብነት ወደ ሰፊነት ወዘተ.. መሄድና መሆን እየቀረ፥ወደ ተቃራኒው አዘቅት በመግባት እንኳን ሀገር ወዳድነት ቀርቶ የግል ማንነት እንኳ ሊገኝ አይችልም።

ሀገር መውደድ ሲባል በዕምነት ይሁን በተግባር ደረጃ ሲፈረጅ፥ በአንድ መልካ ምድራዊ ክልል ተወስኖ በሚገኝ ሀገር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን፥ ዜጎቹንም፥ የዜጎቹንም፥ክብር፥ ሰብዕና፥ ነፃነትና ታሪክ፥ ባኅልና ጥቅም ሁሉ አክብሮ የሚያስከብር፥ ለዚህም ሲባል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አይከፍሉ መሥዋዕትን መክፈልን የሚጠይቅ ነው። ሀገር መውደድ ከሕዝብ ተገንጥሎ የሚታይ ክስተት ሳይሆን ሀገርንና ሕዝብ በአቀፈ ሁለንተናዊነት ዙሪያ የሚሽከረከር ህያውነትና የኅላዌውም መግለጫ ክስተት ነው። ማነኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ለሚወደውና ለሚሳሳለት ሁሉ የመጨረሻ ፍቅሩን የሚገልጽለት ዋጋ ከሕይወት የበለጠ ሌላ የሀገር ፍቅር ማረጋገጫ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም። ዛሬ በአብዛኛው መልኩ ሲታይ፥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስሜት እየተሸረሸረ፥ በቦታው የየግለሰቦች የማንነት ፍለጋና ብሎም፥ የእኔ ማንነት ከየትኛው ነው? ወደሚለው የራስ መታወቂያና መግለጫ እየተኬደ ነው። ሌላው ቀርቶ፥ አብዛኛው ማለት ይቻላል፥ የጋራ ጠላት በሆነው በወያኔ ማንነት ላይ እንኳ ተመሳሳይ አመለካከት፥ ግንዛቤና ድምፃሜ ለመድረስ በሚያስቸግርበት ሁኔታ ላይ ነው። አንዱ ወያኔን ወያኔ ሲል፥ ሌላው ህወሓት ማለትን ይመርጣል። የተቀረው ደግሞ፥ ኢሕአዴግ ብሎ ሊጠራው ይፈልጋል። አባባሉ ፥ "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል" ቢመስልም ትርጉሙ ግን፥ ስልቻ ፥ቀልቀሎ፥ ለቆታ ፥አቆማዳ ከመሆን አያልፍም። የዚህ ዓይነቱ ክስተት እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር፥ ብሔራዊ ስሜት እየተሸረሸረረ፥ የሀገር ፍቅር ዕምነት እየላላ፥ሀገር ወዳድነትና ኢትዮጵያዊነት እየሚሸሸሸ ቦታውን ለጎጥና ለአካባቢ ማስብ እየተስፋፋ መሄዱን ይቀጥላል። የሀገር መጥፋትና የሕዝብ መለያየት በአንድ ቀን ዝምበር በሚታወጅ የዘረኞች መንግሥታዊ መመሪያና ትዕዛዝ ፈጥኖ ይከስማል ባይባልም፥ መርዙ በቶሎ ካልተነቀለ፥ ቀስ በቀስ በሄደት እየጠፋ ላለመሄዱ ግን ምንም ዋስትና ሊኖር አይችልም።

በአሁኗ ኢትዮጵያ ሁኔታ ፥ ማለትም፥ ከወያኔ ሕገ መንግሥት ተብዬው ሰነድ ጀምሮ፥ ሕገ መንግሥቱንም ተንተርሰው የሚወጡት ሕጎች፥ መመሪያዎች፥ መንግስታዊ መዋቅሮች፥ በክልል መዋቅር ላይ ተንተርሰው የወጡት ሥርዓት ትምህርቶችና የመማሪያ መጻሕፍት፥ ዜጎች ከኢትዮጵያ እንዲገነጠሉ የሚፈቅድላቸው የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39ና የወያኔ ዘረኛ የፕሮፓጋንዳ መርሆች ሁሉ ለተከታተለው ዜጋ፥ የሀገሪቱ የወደፊት ዕድል ወዴት እንደሚያመራ ማወቅ አይሳነውም። የዚያች ሀገር ዕድል ነገ ምን መሆን እንዳለበት የወሰነው የወያኔ ዘረኛና አጥፊ ሥርዓት ዕቅዱ እንዳይሳካለት ዛሬ በርትተው ማክሸፍ የሚገባቸው ሀገር ወዳድ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንደሆኑ ሊገነዘቡት ይገባል። ሀገር ወዳድ መሪዎች ስንል በሁለንተናዊ መልኩና በማነኛውም ረድፍ፥ የሀገሪቱንና የሕዝቧን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ ሌት

ተቀን ተግተው የሚሰሩና የሚታገሉ ማለታችን ነው፡፡ ይህንንም ዕውን ለማድረግ ብሎም አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት፥ የሀገር ነፃነት፥ የሕዝብ ብሄራዊ ጥቅምና አንድነት የሚጠይቀውን የሕይወት ዋጋ ለመክፍል የተዘጋጁ ማለታችን ነው፡፡ በኢሕአፓ ዕምነትና ተመክሮ የሀገር ወዳድነት ዓርማው አንድ ብቻ ነው፡፡ ሀገሪቱንም የሚያይበት መነፅር እንደዚሁ አንድ ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ዜጎችና ብሔራዊ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ፥ ማስከበርና ለዚህም ዓላማና ግብ እየታገሉ መሰዋት፡፡ ሀገራችንን እስከ ችግሯና ደስታዋ፥ ድኅነቷና ብልፅግናዋ፥ ህመሟና ጤንነቷ፥ ብርታቷና ድክመቷ፥ ወዘተ ከመውደድ፥ ከማፍቀርና ሕዝቧንም ከማክበር የተለየ ራዕይና ተስፋ የለንም፡፡ ሀገራችንን በክፉ ቀን አጋልጠን፥ በመከራዋ ጊዜ ከድተን፥ በቀውጢ ቀን ሸሽተን፥ ለበላ-ዒሰብ አጋልጠን አንተዋትም፡፡ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ታጋዮች እስካገኘን ድረስ ኃይላችን አስተባብረን፥ አቅማችን አቀናጅተን፥ ተመክሯችንን አካፍለን ከወያኔ መንጋጋ በማውጣት ከጥፋት እናድናታለን፡፡ ለጊዚያዊ የምርጫ ተሳትፎ ብለን፥ ለሚያስተዛዝብ ወቅታዊ ጥቅም ብለን፥ ኢትዮጵያዊ ብኩርናችንን ለአላፊ ጠፊ ጥቅማ ጥቅም አንደራደርም፡፡ ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ዜጎችና አይበገሬ ታጋይ አርበኞች ከሁሉም በላይና ከማነኛው ጉዳይ አስቀድሞ የሀገራቸውንና የሕዝባቸው ብሔራዊ ጥቅም የሚያስቀድሙ መሆናቸውን ከልብ ስለምንረዳ ሰልፋችንን ከእነርሱ ጋር አጣምረን ከመታገል በቀር ሌላ የቅርብም ሆነ የሩቅ አጀንዳ የለንም፡፡ ይህን ከማድረግ ደግሞ የሚያግደን ኃይል እንደሌለ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፥ የወያኔ መሪዎችም ቢሆን ሳይወዱ በግድ አምነው የተቀበሉት ሀቅ ነው፡፡

ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ለሀገሩ ዘብ ይቁም!!